# በደቡብ ጎንደር አንድ የቅንጅት አባል ተገደለ

በደቡብ ጎንደር ዞን በፎገራ ወረዳ ወረታ ከተማ ውስጥ መልካሙ ክንድ አለም የተባለ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባል ሐምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ተገደለ፡ ፡

ይህን 21 ዓመት ዕድሜ የነበረውን ወጣት ሕይወት ያጠፉ ነፍሰ ገዳዮች እየተዝናኑ ሲሄዱ ህብረተሰቡ ለፖሊስ ቢጠቁሙም ፖሊሶች ግለሰቦቹን ለመያዝ ፈቃደኛ ሳይሆኑ እንደ ቀሩ ለማወቅ ተችሏል።

ወጣት መልካሙ በምርጫ 97 በወረታ ከተማ በታዛቢነት ተመድቦ የገዥው ፓርቲ አገልጋዮች ምርጫውን እንዳያጭበረብሩ ከፍተኛ ትግል ማድረጉ ታውቋል።

የወጣት መልካሙ የቀብር ሥነሥርዓት በደቡብ ጎንደር በፋርጣ ወረዳ በምንዳጎ ተክለሐይማኖት ቤተክርስቲያን ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ተፈፅሟል።

# አንድ የቅንጅት ደጋፊን የገደለው እጁን ሰጠ

በደቡብ ኢትዮጵያ በጌዴኦ ዞን በዲላ ዙሪያ ወረዳ በዋካሜ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ቱሬ ዲኦ የተባሉትን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ደጋፊን ሐምሌ 5 ቀን 2000 ዓ.ም በጥይት ገድሎ የተሰወረው ለማ የተባለ የሥርዓተ አገዛዙ የቀበሌ ታጣቂ ከሕግ ሊያመልጥ እንደማይችል አውቆ ሰሞኑን በሲዳማ ዞን ለጭኮ ወረዳ ፖሊስ እጁን ሰጠ።

በሥልጣን ላይ ካለው አገዛዝ የማምለክን ያህል ፍቅር የነበረው ይህ ነፍሰ ገዳይ ወንጀሉን ፈፅሞ እስከ ተሰወረበት ዕለት ድረስ በዲላ ዙሪያ ወረዳ በዋካሜ ቀበሌ ማህበር ውስጥ የጦር መሣሪያ ታጥቆ ንፁሐን ዜጎችን ሲያፈራራ የኖረ መሆኑ ታውቋል።

ግለሰቡ ቱሬ ዲኦን በጦር መሣሪያ መግደሉ እንደተሰማ የዲላና የአካባቢው ሕዝብ በቁጣ ገንፍሎ ወደ መኖሪያ ቤቱ በማምራት ቤቱን አፈራርሶ እንዳልነበረ ማድረጉንም ለማወቅ ተችሏል።

የቱሬ ዲኦ የቀብር ሥነ ሥርዓት በጌዴኦ ዞን በአባያ ወረዳ በሜኤሣ ቀበሌ ውስጥ ሐምሌ 6 ቀን 2000 ዓ.ም መፈፀሙ ታውቋል።

አንዳንድ የዲላ ከተማ ነዋሪዎች በጌዴኦ ዞን ውስጥ ንፁሐን ዜጎች በየወቅቱ በአገዛዙ ቅጥረኛ አገልጋዮች መገደላቸው ክፉኛ ያስቆጣቸው መሆኑንም ተናግረዋል።

ቀደም ሲል በዚሁ ዞን በወናጎ ወረዳ በወናጎ ከተማ አስቻለው ባዬ የተባለ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባል ባንድ ቅጥረኛ ፖሊስ ሲገደል እንዲሁም መሐመድ

የተባለ የቅንጅት ፓርቲ ደጋሬ በዚሁ በወናጎ ከተማ ባሻ ተረፈ ኡዴ በተባለ ፖሊስ በተተኰሰ ጥይት እግሩን መሰበሩ ይታወሳል።

EthioLion.Com